# እውነት ትግራይ መሬት ቆርሳ ወስዳለችን ?

## ሀቅ ለፈለገ ሀቁ ይህ ነው

## 1 መግብያ

ተከበራቹ አንባብያን ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ የገፋፋኝ ነገር አሁን ወቅት በአማራ ክልል ይነሳ ያለው የወሰን እና የማንነት ጉዳይ ነው፡፡ የወልቃይት ጉዳይ አዲስ ክስተት ስለሆነ አይደለም፡፡ የወልቃይት የራያ ጉዳይ ተሰምቶ ስለማያውቅም አሁን አዲስ ተአምር ስለተፈጠረ አይደለም፡፡ አሁን ያለው የፌደራል ስርዓት የማይዋጥላቸው የትምክህት ሓይሎች ሁሌም ሲያነሱት የነበረ ነገርግን ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ብዙም እንደ ትልቅ አጀንዳ አይታይም ነበር፡፡ ምክንያቱ ህዝቡም አመራሩም በትክክል ይገነዘበው ስለነበር፡፡ ***ታድያ አሁን ምን ተፈጥሮ ነው የራያና የወልቃይት ጉዳይ በጎንደር፣ ባህርዳር እና ሌሎች ትላልቅ የአማራ ከተሞች መነጋገሪያ ሆኖ ሰላማዊ ሰልፍ እስከ ማድረግ የደረሰው?*** ባለቤቶቹ (ራያና ወልቃይት ህዝቦች) ምንም ጥያቄ ሳይጠይቁ በጎንደር እና በባህርዳር ብሎም በአዲስ አበባ ሆኖ የማንነት ጥያቄ መጠየቅስ ምን አመጣው የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ በማሰብ ነው ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ የተገፋፋሁት፡፡

*ማሳሰብያ፡- በዚህ ፅሁፍ ይሁን በሁሉም ከህዳሴ ኢትዮጵያ የሚመነጩ ፖለቲካዊ ፅሁፎች ትምክህት፣ ነፍጠኛ እና ጠባብነት የሚል በስፋት የምጠቀም ሲሆን፣ የዚህ ትርጉም ትምክህት እና ነፍጠኛ በምልበት ጊዜ የአማራ ህዝብ እና ገዢዎች ለመለየት እንደሆነ፣ ጠባብነት በምልበት ጊዜ በብሄራዊ ጭቆና የተሰቃዩ ህዝቦች እና ይህን ተገን አድርገው በመታገል የፀረ ህዝብ እና ፀረ ዴሞክራሲ ዓላማ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ሀይሎች ለመለየት ነው፡፡ ትምክህት ማለት ከአማራ ህዝብ አብራክ የወጡ ገዢዎች እና የነሱ አመለካከት ተጋሪዎች ሲሆኑ ጠባብ የሚባሉት ደግሞ*



ህዳሴ ኢትዮጵያ

hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

***ከትግራይ ከኦሮሞ፣ ከደቡብ ህዝቦች፣ እና ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች አብራክ የወጡ የመነጠል ወይም የራሳቸው የበላይነት የሚሰብኩ ሀይሎችን ለማመላከት ነው፡፡ በዚህ ፅሁፍ ትምክት፣ ነፍጠኛ፣ ጠባብ ወይም ኪራይ ሰብሳቢ ማንም ህዝብ አይወክልም፡፡***

## *1.1 አኩሪ የኢትዮጵያ ታሪካችን*

አገራችን ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ እና የሰው ልጅ ስልጣኔ ከተጀመረባቸው አገሮች አንዳ እንደሆነች የታሪክ አሻራዎችዋ ይመሰክራሉ፡፡ በዓለማችን ዘመናዊ የመንግስት አስተዳደር ከጀመሩት ጥቂት ሰርወ-መንግስታት አንዱ አገራችን ኢትዮጵያ እንደሆነች የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ፡፡ የኢትዮጵያዊነት ኩራት ተብለው በዓለም የታሪክ መዝገብ የተመዘገበ አንዱ መገለጫችን ደግሞ የመጣውን ባዕድ ወራሪ ሀይል አይቀጡ ቅጣት በመቅታት አሳፍሮ መስደድ አንዱ ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢትዮጵያ በአፍሪካ የነፃነት ተምሳሌት ተደርጋ በመውሰድ ልዩ ቦታ የሚሰጣት፡፡ ይህም በታሪክ ብቻ የሚነገር ሳይሆን፣ በደም እና በዘር የተላለፈ እስኪመስል ድረስ በኛ ትውልድም የተቃጡብን ወረራዎች በከፍተኛ መስዋእትነት እና በፅናት ስንመክታቸው መቆየታችን ምን ያክል የወረስነውን ጀግንነት አቅበን እየተጓዝን ያለ መሆናችን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውጭ ጠላትን ብቻ ሳይሆን የውስጥ ጭቆናም በመቃወም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በግል፣ በቡድን እንዲሁም በተደራጀ በመታገል ከፍተኛ መስዋእትነት የሚከፍል ህዝብ ሆኖ በስተመጨረሻ ለአንድ መቶ ዓመታት ህዝብን ሲያሰቃይ የነበረው የትምክህት ስርዓት ላንዴና ለመጨረሻጊዜ እንዲንኮታኮት አድርጓል፡፡ ይህን የጀግንነት እና የአደራ ተቀባይነት ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

## *1.2 አሳፋሪ የኢትዮጵያ ታሪካችን*

በሌላ በኩል ደግሞ ልክ እንደ አኩሪ ታሪካችን፣ ***<u>እንደ ኢትዮጵያውያን በአደባባይ የምናፍርበት እና የምንሸማቀቅበት ታሪክም አለን፡፡</u>*** እሱም የዓለማችን ስልጣኔ



*ህዳሴ ኢትዮጵያ*

*hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com*

ጀማሪዎች፣ የዓለማችን ዘመናዊ መንግስት ጀማሪዎች እንዳልነበርን ይህ ገናናነት ከዘመናት ወደ ዘመናት እየተሸረሸረ መጥቶ በአሁኑ ደረጃ በዓለማችን በድህነት ከሚጠቀሱ አገሮች አንድዋ ለመሆን አብቅቶናል፡፡ ይህ አሳፋሪ ታሪክ ካልተቀየረ የአባቶቻችን ጀግንነት እየጠራን መኖር ሩቅ አይወስደንም፡፡ መበታተናችን ነው፡፡ ለዚህም ብዙ ሳይንሳዊ ትንተና ሳያስፈልገው ከ27 ዓመት በፊት መለስ ብሎ ማስታወስ በቂ ይመስለኛል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የተለገሳት የብዙሃን አገር፣ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች፣ የብዙ ሃይማኖቶች እና እምነቶች አገር እያለች፤ ባለፉት አንድ መቶ ዓመት የነበሩትን የአሀዳዊ ስርዓት አራማጅ የዘውዳዊና የደርግ ስርአቶች ይህን ነባራዊ ሁኔታ /ብዙሀነት/ በመካድ አንድ ኢትዮጵያ፣ አንድ ህዝብ፣ አንድ ሀይማኖት በማለት ሚሊዮኖች ህዝቦች በመጨፍለቅ ሲያሰቃይ አገራችን በስልጣኔ ገናና እንዳልነበረች የዓለማችን ጭራ ለመሆን መብቃትዋ በአሳፋሪነት ሊገለፅ የሚችል ታሪካችን ነው፡፡

## 1.3 የመገንጠል ጥያቄና አፈታቱ

ደርግ በተባበረ የህዝቦች ትግል ግብአተ መሬቱ በ1983 ዓ.ም. ግንቦት 20 ሲፈፀም በርካታ የታጠቁ የብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ድርጅቶች የነበሩ ሲሆን አብዛኞቹ መበታተንን፣ ነፃነትን የሚሹ ነበር፡፡ እነዚህ የታጠቁ ሀይሎች በዛን ጊዜ ያራምዱት የነበረ አመለካከት ሲታይ፣ *በስመ አንድ-አገር አንድ-ህዝብ አንድ-ሀይማኖት ማንነታችን በማዋረድ ደብቀን ከመኖር፤ እንደ ሁለተኛና ሶስተኛ ዜጋ ሆኖ ከመኖር መበተን ይሻለናል የሚል ምርጫ የሚመርጡበት ጊዜ ነበር፡፡* በዚህ ጊዜ ኢህአዴግ ባደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ፣ የትምክህት ስርዓት ስላከተመ ሁላችንም ይሆነናል የምንለው በህዝብ ይሁንታ የሚመራ መንግስት ለመመስረት በጋራ እንነሳ በማለቱ እና የሽግግር መንግስት በመመስረቱ የመነጠል አጀንዳቸው በይደር በማስቆየት በሽግግር መንግስት የራሳቸው አስተዋፅኦ በማድረግ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ



*ህዳሴ ኢትዮጵያ*

*hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com*

ዘመናዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና የህዝቡ ተሳትፎና ይሁንታ ያለበት ህገመንግስት ለማፅደቅ በቃን፡፡

በዚህ ምክንያት ነበር የአብዛኛው የመነጠል ፍላጎት በህገመንግስቱ መሰረት በክልል እና ራስ በራስ አስተዳደር ተግባራዊ በማድረግ ጥያቄውን ረገብ እንዲል የቻለው፡ ፡ በዛን ጊዜ የተወሰኑ እንደ ኦነግ በሁኔታውና ሂደቱ እርካታ ያጡ ሰላማዊ መንገዱ ትተው ወደ በረሀ እና ወደ ውጭ አገር የሄዱ ቢሆንም አብዛኞቹ /ከ75 በላይ ድርጅቶች/ በህገመንግስቱ መሰረት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል ለማድረግ በመወሰናቸው እነሆ አሁን ለደረስንበት የዴሞክራሲ ደረጃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው፡፡

***<u>ህገመንግስቱ ከረቀቀ ቦኋላ፣ ከመፅደቁ በፊት ወደ ህዝቡ ወርዶ ነፃና ግልፅ ውይይት የተደረገበት ሲሆን በዚህ ላይ ከ18 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆኑ ከ18 ሚልዮን በላይ ዜጎች በውይይቱ እንደተሳተፉ ሰነዶች ያሳያሉ፡፡ በዚህ መሰረት በህገመንግስቱ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የያዘ ሲሆን ከዚ ፅሁፍ ዓላማ አኳያ ግን ስለ የክልሎች አከላለል እና መብት የተቀመጡትን ነገሮች በማውሳት ከወልቃይት እና ራያ ጉዳይ በማያያዝ ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡</u>***

## 2 የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት

ኢትዮጵያ ከሶስት ሺ ዓመታት በላይ የዘለቀ ዕድሜ ጠገብ የመንግስትነት ታሪክ ያላት ቢሆንም አሁን ያላት ቅርፅ የያዘችው ግን በዘመነ አፄ ሚኒሊክ ከ120 ዓመታት በፊት ጀምሮ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘ እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ፡፡



*hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com*




***ስዕል 1 ጥንታዊ የኢትዮጵያ ግዛት***

This map, dating from the 1570s, still takes Europe's devout wishes for geopolitical truth. It was produced in Antwerp by Ortelius, entitled *A Description of* ***The Empire of Prester John, Also Known as the Abyssinian Empire***.

ከዛ በፊት የነበረውን የግዛት ወሰን ሲታይ አንዴ የሚሰፋ ሌላ ጊዜ የሚጠብ የነበረ እንደሆነ የአቢሲኒያ ካርታዎች ያሳያሉ፡፡ አንድ ወቅት እስከ መካከለኛው አፍሪካ የሚለጠጥ የነበረ ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ እስከ ባህር ማዶ የመን ድረስ በመዝለቅ ግብር ይሰበሰብ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡



*ስዕል 2 ጥንታዊ ለኢትዮጵያ ግብር የሚገብሩ ቦታዎች*

ይሁንና አሁን የያዘችው የግዛት ወሰን ግን በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት ከጎሮቤቶቻችን ባዕድ ገገርዎቻቸው ጋር በተለምዶ በ1902 እና 1908 ስምምነት እየተባለ የሚገለፁ ስምምነቶች መሰረት የተካለለ እና እስከ አሁን ድረስ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ የግዛት ወሰን ነው፡፡

# 3 የትግራይ አስተዳደር አካለል

የአገር ውስጥ አከላለል ሲታይ ደግሞ የተለያዩ የአስተዳደር አከላለል የነበረ ሲሆን አንዴ በጠቅላይ ግዛት ሌላ ጊዜ በክፍለ ሀገር የሚታወቅ ነበር፡፡ በአፄ ሚኒሊክ እና በአፄ ኋ/ሥላሤ ዘመነ መንግስት ይደረጉ የነበሩ አከላለል ሲታይ ለስርዓቱ በሚበጅ መንገድ ነበር፡፡ ለስርዓቱ በሚበጅ ሲባል ስርዓቱ የአስተዳዳር እና የፀጥታ ጉዳዮች በሚመች፣ ለግብር አሰባሰብ በሚመች፣ የህዝብን ጥያቄ እና መነሳሳትን ለማፈን በሚያስችል ሁኔታ የሚደረግ ነው የነበረው፡፡ በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር ቦታዎች ማለትም ጠቅላይ ግዛት፣ አውራጃ፣ ወረዳ እና ከዛ በታች የነበሩ የአስተዳደር እርከኖች ገገርዎች እና አስተዳዳሪዎች አሿሿም ደግሞ ለዚህ ዓላማቸው የሚጠቅምና ለስርዓቱ ያላቸውን ታማኝነት እየተመረጠ ነበር የሚሾመው፡፡

## *3.1 ከአፄ ሚኒሊክ በፊት የትግራይ የግዛት ወሰን*

አፄ ሚኒሊክ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከመሆናቸው በፊት ትግራይ ተብሎ የሚታወቅ ግዛት በሰሜን የኤርትራ ቦታዎች ያካተተ ሲሆን በደቡብ ደግሞ በወሎ አይሎሃ ምላሽ በጎንደር ለማሊሞ እምባ ጊወርግስ ድረስ የሚዘልቅ እንደነበር ይታወቃል፡፡ አፄ ሚኒሊክ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከሆኑ በኋላ ግን በምእራብ ትግራይ በኩል ያለውን ሰፊ መሬት ማለትም ዙርያው 807 ኪ.ሜ. የሆነው 25793 ስኳር ኪሎሜትር ስፋት ያለው የትግራይ ቦታ ቆርሶ ወደ ጎንደር ማካለሉ ታሪክ መዝግቦታል፡፡ ተቆርሶ የተወሰደው የአስተዳደር ወሰን በጎግል ካርታ ሲታይ እንደሚከተለው ይመስላል፡፡




*ስዕል 3 ቅድመ አፄ ሚኒሊክ የትግራይ የግዛት ወሰን*

ኤርትራን ሳይጨምር የትግራይ ካርታ ስፋቱ 114000 ስኴር ኪሎሜትር እንደነበር ከጎግል የተወሰደ ልኬት ያሳያል፡፡




*ስዕል 4 በአፄ ሚኒሊክ  ተቆርሶ ወደ ጎንደር የተካለለው የትግራይ የግዛት ወሰን*

የትግራይ ካርታ አፄ ሚኒሊክ 25.8 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. ቆርሶ ወደ ጎንደር ካካለለ በኋላ የነበረው የትግራይ ቅርፅ እንደሚከተለው ይመስል ነበር፡፡




***ስዕል 5 በአፄ ሚኒሊክ ዘመን የትግራይ የግዛት ወሰን***

ከስዕሉ እንደሚታየው አፄ ሚኒሊክ በሚያስተዳድራት ኢትዮጵያ የትግራይ ግዛት በአማካይ 1388 ኪ.ሜ. ዙርያ ያለው 85378 ስኴር ኪሎሜትር ስፋት እንደነበረው ያሳያል፡፡

## *3.2 በዘመነ ኋ/ስላሴ የትግራይ የወሰን ግዛት*

የትግራይ ህዝብ እላይ ላዩ ይደርስ የነበረውን አስከፊ ጭቆና በተናጠልም በቡድንም መልክ በመቃወም በዘውዳዊ ስርዓት ላይ ያነጣጠረ ህዝባዊ አመፅ በስፋት ይታይ የነበረ ቢሆንም፣ በተለይ በዘመነ ኋ/ስላሴ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ከደቡባዊ ትግራይ ጀምሮ እስከ ምስራቃዊና ማእከላዊ ትግራይን ያዳረሰ ከፍተኛ የህዝብ መነሳሳትና ዓመፅ ፈጥሮ የዘውዳዊ ስርዓት ከትግራይ ጠራርጎ ያወጣው ሲሆን የዘውዳዊው ስርዓት ከስረ-መሰረቱ ያናጋ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ ይህን ማዕበል ተከትሎ የንጉስ ኋ/ስላሴ ዘውዳዊ መንግስት ከፍተኛ አደጋ ላይ በመውደቁ፣

ከኢንግሊዝ መንግስት ድጋፍ በመጠየቅ የህዝቡን መነሳሳት በኢንግሊዝ አውሮፕላን ከየመን እየተነሱ ባደረጉት አስነዋሪና አሰቃቂ ጭፍጨፋ የህዝቡ ዓመፅ ለጊዜው እንዲበርድ እና እንዲበተን አድርጎታል፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የንጉሱ ድምዳሜ ***"ትግሬ አንድ ላይ ሆኖ የተረጋጋ ስልጣን አይኖረንም ስለዚህ የህዝቡ ተቋውሞ ለመቆጣጠር ከፋፍለን መግዛት ይኖርብናል"*** የሚል ድምዳሜ ተደረሰ፡፡ በዚህ ድምዳሜ መሰረት የንጉስ ኋ/ስላሴ መንግስት ልክ እንደ ኣፄ ሚኒሊክ በወልቃይት ያደረጉት፣ የተወሰነ የራያ አከባቢ ወደ ወሎ በማካለል የትግራይ ህዝብ በሶስት ቦታ (በጎንደር፣ በዎሎ እና በትግራይ) እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ የተደረገው ማካለል እስከ ደርግ ስርዓት የቀጠለ ሲሆን ካርታውም እንደሚከተለው ይመስል ነበር፡-




*ስዕል 6 በአፄ ሀ/ስላሴ እና በደርግ ዘመን የትግራይ የግዛት ወሰን*

በትግራይ ቀዳማይ ወያነ አመፅ ሲስነሳ በኢንግሊዝ መንግስት አውሮፕላኖች በመደብደብ አመፁ ለማስቆም የተቻለ ሲሆን ከዛ ጊዜ ጀምሮ የትግራይ ህዝብ በሶስት ቦታ መከፈል ብቻ ሳይሆን፤ የተቀረው ትግራይ ተረጋግቶ እንዳይኖር እና ሌላ ተጨማሪ ዓመፅ እንዳያስነሳ በማለት የትግራይ ገዢዎችን እርስ በርሳቸው ማጣላት፣ ህዝቡ በአውራጃ እየተከፋፈለ እንዲናቆር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

ከታችያለው ስዕል እስከ ደርግ ውድቀት ጊዜ የነበረ የትግራይ ግዛት ክልል ሲሆን ዙርያው 1262 ኪ.ሜ. ሆኖ ስፋቱ ደግሞ 61054 ስኴር ኪሎሜትር ነበር፡፡ ይህ ካርታ




*ስዕል 7 ከቀዳማይ ወያነ ቦኋላ እስከ የደርግ ስርዓት መውደቅ ጊዜ የነበረ የትግራይ ካርታ እና የቆዳ ስፋት የሚያሳይ ምስል*




***ስዕል 8 በአፄ ሀ/ስላሴ ተቆርሶ የተወሰደ የትግራይ የግዛት ወሰን***

እላይ እንደሚታየው በቀዳማይ ወያነ የህዝብ ዓመፅ በመነሳቱ ምክንያት ህዝቡን ከፋፍሎ ለመግዛት በማሰብ 980 ኪሎሜትር ዙርያ ያለው ስፋቱ 25261 ስኴር ኪሎሜትር ወይም 30% ከነበረው የትግራይ ቦታ በመቁረስ ወደ ወሎ እና ጎንደር እንዲካተት ተደርጓል፡፡ *በዚህ መሰረት እስከ የደርግ ስርዓት መገርሰስ ድረስ የትግራይ የቆዳ ስፋት 61054 ስኴር ኪሎሜትር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህ ማለት በጎንደር አዋሳኝ ከተከዜ ወንዝ ምላሽ ሲሆን ከወሎ ደግሞ ከማይጨው አከባቢ ከምትገኝ የመስዋእት ወይም ችንኮ-ማጆ የሚባል አከባቢ ሆኖ የአፋር ቦታዎች እንዳሉ በማካለል እስከ ኤርትራ ድንበር ነበር የተካለለው፡፡*

## 3.3 አሁን ያለው የትግራይ ኣካላለል

### 3.3.1 ህወሓት ይታገልለት የነበረ የትግራይ ወሰን

የደርግ ስርዓት ወደ ስልጣን ከመጣ ቦሃላ ሁሉም የሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በግላጭ በኣዋጅ ሲያፍናቸው *በርካታ የኢትዮጵያ ተራማጅ ሃይሎች ደርግን ለመፋለም በረሃ መውጣታቸው ይታወቃል፡፡* ከነዚህ ተራማጅ ሀይሎች ውስጥ ህወሓት በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ህወሓት ለትጥቅ ትግል በረሀ

ሲወጣ ብሄራዊ ጭቆና እንደ ዋነኛ ጥያቄ አድርጎ የተነሳ የነበረ ሲሆን በዛን ግዜ የትግራይ ህዝብ ከብሄራዊ ጭቆና በማላቀቅ ከወንድም የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ለመመስረት የሚል ዓላማ ይዞ ተነስቷል፡፡ በዚህ ጊዜ የትግራይ ብሄራዊ ጭቆና ለማራገፍ ሲታገል ***የትግራይ ድንበር ብሎ የወሰደው በታሪካዊ አመጣጡ ላይ ተመስርቶ 5 ብሄር የያዘ ማለትም ትግራይ ብሄር፣ አፋር ብሄር፣ አገው ብሄር፣ ሳሆ /ኢሮብ/ ብሄር እና ኩናማ ብሄር ያካተተ ነበር፡፡*** በዚህ ጊዜ የነበረው ካርታ ሲታይ እንደሚከተለው ይመስላል፡-




*ስዕል 9 አምስቱ ብሄር ያጠቃለለ የትግራይ የግዛት ወሰን*

***በዚህ መሰረት በህወሓት ስር ተጠልለው ይታገሉ የነበሩ ህዝቦች ሲታይ የትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ የአምስቱም ብሄር ህዝቦች ነበሩ፡፡***

እንግዲያውስ ይህ ነበር የትግራይ ህዝብ የትግል መነሻ፡፡ ስለዚ ህወሓት ደርግን ለመደምሰስ ብሎ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ የወልቃይት፣ የራያ፣ የአፋር፣ የሳሆ /በዛን ጊዜ ሳሆ የአሁኑ ኢሮብ/ እንዲሁም የኩናማ ብሄር ህዝቦች በህወሓት ስር ታቅፈው እንደ ታጋይ፣ እንደ ሚሊሻ ሆኖው ከፍተኛ መስዋእት ከፍለዋል፡፡ ስለዚህ ነው የራያና የወልቃይት ህዝብ በህወሓት ስር ተደራጅቶ በሚኒሊክ እና በአፄ ሃ/ስላሴ የተረገጠ ማንነታቸው እና ሳይወዱ ከብሄራቸው ተለይተው እንዲተዳደሩ የተደረገውን ለመመለስ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል የሚባለው፡፡ ለዚህ ነው የራያና የወልቃይት ህዝብ በመራራ ትግሉ አሽቀንጥሮ የጣላቸው የትምክህት ሃይሎች አሁን ህይወት ዘርተው በአዲስ አበባ እና በጎንደር መሽገው ስለ ራያና ወልቃይት ጠበቃ መስለው ለመታየት እየሞከሩ ነው የሚባለው፡፡

## 3.3.2 በህገመንግስቱ መሰረት አሁን ያለው የትግራይ የግዛት ወሰን

አሁን ያለው አለላለል ታሪካዊ ይዞታ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት የብሄር እና ቋንቋ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ፣ ባህልና ትስስር መሰረት በማድረግ የተካለለ ሲሆን፣ ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት ለመተግበር የሚያስቸግሩ እና አከራካሪ የሆኑ አከባቢዎች በህዝበ ውሳኔ ወይም ምርጫ እንዲካለል ተደርጓል፡፡ ለንፅፅር እንዲያመች ስዕሉ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡




*ስዕል 10 በህገመንግስቱ መሰረት የተካለለ የትግራይ ክልል ወሰን*

ከደርግ ውድቀት በሃላ ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት የተደረገው አከላለል፣ የትግራይ ክልል የቆዳ ስፋት እና ዙሪያ ሲታይ እላይ በስእሉ እንደሚታየው ዙርያ 1485 ኪ.ሜ. ሲሆን ስፋቱ ደግሞ 53036 ስኴር ኪ.ሜ. ሆኖዋል፡ ፡

### 3.3.3 የህገ-መንግስቱ መስፈርት እና አሁን ያለው የትግራይ የአስተዳደር ወሰን

*የትግራይ ታሪካዊ ካርታ እንደሚያሳየው 114000 ስኴር ኪሎሜትር ነው አሁን ያለው ግን 53 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. ነው ታድያ 61 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. ወይም 54% የትግራይ ግዛት የት ገባ?* መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡

አሁን ታሪካዊ አከላለል ብቻ እንደ መስፈርት በመውሰድ ትምክህተኞች በሚያነሱት የራያና የወልቃይት ጥያቄ መርሆ ተከትለን ስናየው፤ የትግራይ ክልል የመሬት ስፋት 114 ሺ መሆን ነበረበት፡፡ አነጋገር አሁን ወደ ሌላ ክልል የተካለለው 61 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. ወደ ትግራይ መካለል የሚገባው ነው፡፡ ልዩነቱ ነፍጠኞች የሚሉት የትግራይ ግዛት በደርግ የነበረ ብቻ መሆን አለበት ስለሚሉ ነው፡፡ ***ነገር ግን ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መርሆ አሁን ያለው የትግራይ ካርታ ሲታይ ህወሓት ትግል ሲጀምር የነደፈው ሳይሆን ደርግ ከተደመሰሰ በሃላ ከኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ በመምከር የተደረሰ ስምምነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንዴት?*** በሶስት መንገዶች

1. በህገመንግስቱ መሰረት ***የአፋር ብሄር ካለው የህዝብ ብዛት እና የቆዳ ስፋት ሲታይ እንደ ብሄር በአንድ ክልል መካለል ስለነበረበር በትግራይ ላይ የነበረው ሰፊ ቦታ ከብሄረሰቡ ጋር እንዲካለል ተደርጓል፡፡*** በዚህ መሰረት እታች ስዕሉ እንደሚታየው 1009 ኪ.ሜ. ዙርያ ያለው 43887 ስኴር ኪ.ሜ. ስፋት ያለው ቦታ ድሮ በታሪክ የትግራይ ተብሎ ከሚታወቀው በማስወጣት ወደ ***አዲስ የአፋር ክልል በመካለሉ፡፡***
2. ሌላው ምክንያት ደግሞ በትግራይ ታሪካዊ አመጣጥ በማእከላዊ ደቡብ ትግራይ ኣከባቢ ይኖሩ የነበሩ ***የትግራይ አገው ብሄር በብዛታቸው ኣኳያ ሲታይ በአማራ ውስጥ ያሉ የአገው ብሄር ህዝብ ስለሚበዙ የትግራይ ኣገው ወደ ኣማራ እንዲካለሉ ማድረግ ሁለተኛው ምክንያት ነው፡፡***
3. ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ በተለይ አይሎሀ-ምላሽ እና እምባ ጊወርግስ-ምላሽ ሲታይ፣ ምንም እንኳ በታሪካዊ አመጣጡ የትግራይ ቦታ ቢሆንም ግን ደግሞ የህገመንግስቱ መርሆዎች ማለትም የቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ ሲታይ እነዚህ አከባቢዎች የተወሰነው ቦታ የአማራ ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ በስፋት የሚስተወልባቸው ሲሆኑ ገሚሱ ደግሞ የትግራይ ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ በስፋት ሲስተዋልባቸው እመሃል ላይ ደግሞ አጠራጣሪና የሁለቱም ብሄር (የኣማራ እና የትግራይ) ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ

በስፋት የሚታይባቸው ነበሩ፡፡ ***<u>በዚህ መሰረት የማያጠራጥሩ ቦታዎች ማለትም አማርኛ ተናጋሪ የሚበዛበት ወደ አማራ ክልል፣ ትግርኛ ተናጋሪ የሚበዛበት ቦታዎች ወደ ትግራይ ክልል ተካልለዋል፡፡ ለምሳሌ ከእምባ ጊወርግስ እስከ ዓዲ-ረመፅ እና አይሎሀ-ምላሽ እስከ ቆቦ ወደ አማራ ሲካተቱ፣ ወልቃይት-ሑመራ፣ ኮረም፣ አላማጣ ወደ ትግራይ ተካልለዋል፡፡</u>*** በመሃል ላይ ለመለየት የሚያስቸግሩ አንዳንድ ቀበሌዎች እና ጎጦች ደግሞ ***<u>የህዝብ ፍላጎት መሰረት በማድረግ ቀበሌና ከቀበሌ በታች በመውረድ የህዝብ ፍላጎት በመጠየቅ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጎ፡፡</u>*** በዚህ መሰረት ትግርኛ ተናጋሪ እያሉ በአብዛኛው ወደ አማራ በመምረጣቸው ወደ አማራ ክልል የተካለሉ ኣሉ ለምሳሌ በየጭላ አከባቢ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አማራ ተናጋሪ እያሉም ወደ ትግራይ በመምረጣቸው በትግራይ የተካተቱ አሉ፡፡ ይህ ሲደረግ ግን በታሪካዊ አመጣጥ ከኣፄ ሚኒሊክ ዘመነ-መንግስት በፊት የትግራይ የነበረ ቦታ እንጂ የአማራ የነበረ ቦታ አንድም ወደ ትግራይ የመጣ አልነበረም፡፡

***<u>አሁን ያለው የአማራና የትግራይ ክልል የተፈጠረው በዚህ ህገመንግስት ባስቀመጠው መርሆ ተከትሎ የሁሉም ህዝቦች ይሁንታ ታክሎበት የተደረገ እንጂ በአንድ ወገን ወይም ቡድን የተሰራ ስራ አይደለም፡፡ ይህም የህወሓት አመራር፣ የብአዴን ኣመራር በደንብ ያውቆዋል፡፡ ማወቅ ብቻም ሳይሆን ከልቡ የሚያምንበት እና ለህዝበ ውሳኔ ብሎም ባለፉት 27 ዓመታት ይታገልለት የነበረ ጉዳይ ነው፡፡</u>***

# 4 አሁን ያለ የትግራይ አከላለል እና ትርጉሙ

አሁን ያለው የትግራይ ካርታ ከታሪካዊ ይዞታ ሲነፃፀር 54% የግዛት መሬት ወይም በ62184 ስኤር ኪ.ሜ. ያነሰ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት ለህገመንግስት፣ ለዴሞክራሲያዊ አንድነት በማሰብ እንጂ ትምክህተኞች በሚያስቡት ቢሆን እማ 114000 ስኬ.ኪ.ሜ. በተደረገ ነበር፡፡ የትግራይ ህዝብ ለማንነቱ እና ለመብቱ ሲታገል የህዝቦችን መብት ለመንካት ሳይሆን የሌሎች ህዝቦች መብትም ልክ እንደ ራሱ መብት ለማክበርም



*hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com*

ጭምር ነው፡፡ በመሆኑ ስዕል ላይ እንደሚታየው ስፋቱ 62.2 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. የሆነ፤ 2092 ኪሎሜትር ዙርያ ያለው የመሬት ወሰን፣ *ምንም እንኳ በታሪካዊ አመጣጥ የትግራይ ቢሆንም፤* በህገመንግስቱ መስፈርት መሰረት፤ የአፋር እና የአገው ብሄር - በቋንቋ እና ብሄር መስፈርት - እንዲሁም ከእምባ ጊወርግስ እስከ አይሎሃ ምላሽ ያለው አከላለል ደግሞ በህዝብ ፍላጎት መሰረት *ወደ ሌላ ክልል እንዲካለል አድርጓል፡፡*




*ስዕል 11 በህገመንግስቱ መሰረት ወደ ሌላ ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

እላይ ስእል እንደሚያሳየው ከሆነ የትግራይ ህዝብ በከፍተኛ መስዋእትነት ቢሄራዊ ማንነቱ እና መብቱ ካረጋገጠ ቦኋላ በታሪክ የሚያውቀውን 114000 ስኴር ኪሎሜትር ታሪካዊ ወሰኔ ይሰጠኝ አላለም፡፡ የታገለው ብሄራዊ ጭቆና እንዲወገድ እና ወሰን እና ማንነት በህዝቦች ፍላጎት እንዲወሰን ማድረግ ስለነበር፣ ትግራይ የኔ ይዞታ ነው የሚለው ታሪካዊ ቦታው ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ በርካታ የትውልዶች ዓመታት በርካታ ለውጦች

ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ በአጠራጣሪና አከራካሪ ቦታዎች የህዝቡ ውሳኔ እንዲታከልበት ተደርጓል፡፡




*ስዕል 12 በህዝቡ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ እና ፍላጎት መሰረት ወደ አማራ ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

በዚህ መሰረት እላይ በካርታው የሚታየው በቀይ ቀለም የተከለለው ስፍራ በታሪክ ሲታይ የትግራይ ግዛት የነበረ ሲሆን በህገመንግስቱ አካለል መሰረት ***የህዝቡ ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲሁም የአገው ብሄር ህዝቦችም አብዛኛው በአማራ ክልል ስለሚገኙ በትግራይ ውስጥ ይገኙ የነበሩ የአገው ብሄር ህዝብ በአማራ ክልል ሆኖ በጋራ እንዲካለሉ ተደርጓል፡፡***

አሁን የአህዳዊ ስርዓት አቀንቃኞች ታሪካዊ የአስተዳደር አከላለል መሰረት በማድረግ በሚያነሱት ጥያቄ ይፈታ ከተባለ ይቅር ወልቃይት እና ራያ ወደ አማራ ክልል ሊካለል አይሎሀ-ምላሽ፣ አገው ምድር ጨምሮ እስከ እምባ-ጊወርግስ ወደ ትግራይ ክልል ነበር መካለል ያለበት፡፡ ***ነገር ግን ባለፉት 100 ዓመታት የነፍጠኛው ስርዓት ባደረገው ከፍተኛ የዘር እና የማንነት የማጥፋት እንቅስቃሴ*** እላይ በ1163 ኪሎሜትር ዙርያ እና በ18522 ስኴር ኪ.ሜ. ስፋት ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ምንም

እንኳ በታሪክ ትግሬ ቢሆንም /አገው ሳይጨምር ለማለት ነው/፣ <u>በስነ ልቦናም በመዋለድም በስደትም የአማራነት ማንነት እንዲወርሱ በመደረጉ የአከባቢው ነዋሪ በማካለሉ ጉዳይ ወደ አማራ ክልል በመምረጡ ህወሓት እና የትግራይ ህዝብ ምርጫውን በማክበር ተቀብለውታል፡፡</u>




*ስዕል 13 በህዝቡ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ እና ፍላጎት መሰረት ወደ አፋር ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

እላይ የሚታየው ካርታ ደግሞ ዙርያው 1009 ኪ. የሆነ፣ ስፋቱ 43.9 ሺ. ስኴር ኪ.ሜ. የሆነ ቦታ ታሪካዊ አካለሉ የትግራይ ግዛት የነበረ ቢሆንም በዚህ አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ማንነት ሲታይ ግን የአፋር ብሄር ማንነት ያላቸው በመሆኑ፣ የትግራይ ህዝብ የታገለለትንና ከወንድም የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ ያፀደቀውን ህገመንግስታችን መሰረት በትግራይ ውስጥ ይተዳደሩ የነበሩ የአፋር ብሄር ህዝቦች በሌላ የኢትዮጵያ ክፍል ከሚገኙ የአፋር ማንነት ያላቸው ህዝቦች በጋራ የራሳቸው ክልል እንዲፈጥሩና የራሳቸው አስተዳደር እንዲኖራቸው ለማድረግ የአፋር ክልል እንዲመሰርቱ ተደርጓል

ይህ ስለ ትግራይ አከላለል መሰረት ኣድርገን ስለተነሳን እንጂ ይህ የአከላለል መርሆ በመላው አገሪቱ የተደረገ ሲሆን በህገመንግስቱ መሰረት 9 ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት እና 2 የከተማ አስተዳደር ተፈጥሯል፡፡

ይህን አከላለል ከተፈጠረ ጀምሮ *የተወሰኑ አከባቢዎች ክልል መሆን ይገባናል፣ ወረዳ ወይም ልዩ ወረዳ መሆን ይገባናል ቀበሌ መሆን ይገባናል ከሚሉ ውጪ መሰረታዊ የማንነት ጥያቄዎች ሳይቀርቡ ላለፉት 27 ዓመታት አገራችን ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖባት* በህገመንግስቱ 5-ጊዜ የህዝብ ምርጫ በማካሄድ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና በድህነት ማጥፋትና የልማት ጉዞ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ *ለዚህም ነው ማርሽ ቀያሪው መራሹ ኢህአዴግ፣ የኢትዮጵያ የኋልዮሽ ጉዞ በመግታት ወደፊት መራመድ በመጀመሯ አሁን ኢትዮጵያ በዓለማችን ፈጣን የዕድገት ጉዞ ከጀመሩና የዓለም መነጋገሪያ ከሆኑት ጥቂት አገሮች አንዷ ን ለመሆን የበቃችው፡፡* ይሁንና ይህንን ከፍተኛ ዕድገት /የህዳሴ ጉዞ/ ሳይቋረጥ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ቢሆንም አሁንም ወደ ኋላ ሊመልሱን የሚችሉ ችግሮች ከፊታችን ተደቅኖብን ይገኛል፡፡

# 5 ማጠቃለያ

የህዳሴ ጉዟችን ሊያደናቅፉ ከሚችሉት ከፊታችን ከተጋረጡ ችግሮች አንዱ የወሰን፣ የአከላለል፣ እና የማንነት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የአገራችን ታሪክ ብምናይበት ጊዜ ከገናናነት ወደ ጭራነት/አሳፋሪነት ያወረደን ዋነኛው ችግራችን የውስጥ ችግር፣ የመቻቻል ችግር፣ የእኩልነት ችግር፣ የፍትህዊነት ችግር፣ ናቸው፡፡ እነዚህ ችግሮች መፍታት ባለመቻላችን ገዢዎቻችን ሲፈራረቁ ችግሮቹን እያባባሱ፣ በህዝቦች ላይ ችግር እየፈጠሩ ግጭት እየፈጠሩ በመምጣታቸው አመዛኙ የአገራችን ታሪክ በጦርነት ታሪክ የበዛበት እና ህዝባችን በድህነት እና ኋላቀርነት እንዲሰቃይ አድርጓል፡፡



*hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com*

ይህንን ታሪክ ለአንዴና ለመጨረሻጊዜ ለመዝጋት ኢ.ህአዴግ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል ላለፉት 27 ዓመታት በዓለም የዕድገት ታሪክ አገራችን በደማቅ ቀለም ተመዝግባ ትገኛለች፡፡ ይሁንና ይህን ላለፉት 17 ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገብነው በጣም ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለው እና ፍትሃዊ ዕድገት ሊገታ እና ወደኋላ ሊመልስ የሚችል ችግር ገጥሞን እነሆ ላለፉት 3 ዓመታት አገራችን ሰላም እና መረጋጋት አጥታ የህዝቦች ነፃ እንቅስቃሴ ተገድቦ፣ ህገመንግስታዊ መብቶች በጠራራ ፀሀይ በአደባባይ እየተጣሱ ዜጎቻችን በማማረር ላይ ይገኛሉ፡፡

የዚህ ሁሉ ምክንያት የአመራር ዝቅጠት እና መበስበስ ነው፡፡ ይህ ዝቅጠት ገዢው ፓርቲ ኢ.ህአዴግ መሰረታዊ እና የማያዳግም መፍትሂ መስጠት አቅቶት፣ በግምገማና በመሳሰሉት መድረኮች ጥገናዊ ለውጥ እያመጣ በመሂዱ በመጨረሻ ድርጅቱን ለብተና አደጋ የዳረገ ምጥ ላይ በመሰቃየት ላይ ይገኛል፡፡ ከምጡ የሚጠበቀውም ሁለት (Mutually Exclusive outcomes) ውጤቶች ናቸው፡፡ እነሱም

1. ኢ.ህአዴግ ችግሮቹን በደንብ ለይቶ፣ ከራሱ ጋር አጣብቆ Internalize በውስጡ ያቆጠቆጡ ጥገኞችን መንቅሮ በመጣል ትክክለኛ ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መመለስ፤ ወይም ደግሞ
2. ችግሮቹን በውስጡ በማየት ፋንታ ለችግሮቹ ሰበባ ሰበብ እየፈጠረ ወደውጭ በማንጠር Externalize ወይም የውጭ ምክንያት በመፍጠር ከድክመቶቹና ችግሮቹ ጋር አብሮ በመኖር በጥገኛ መንገድ መጓዝ ነው፡፡

**ህዳሴ ኢትዮጵያ**

**ሕዳር 16፣ 2011 ዓ.ም.**

***hidaseethiopia@yahoo.com ወይከዓ hidaseethiopiaa@gmail.com***